18 COMMISSION EARNED

		2011
	Birr	Birr
L/C and other import/export facilities	7,003,808	6,238,853
MTs, TTs, DDs - local and foreign	12,043,719	9,581,017
Letters of guarantee	4,079,612	3,702,931
Cashiers' payment order	1,009,498	1,378,028
Travelers' cheques and others	442,037	637,437
Uncleared effects	1,156,667	1,037,044
	25,735,342	22,575,310

19 OTHER INCOME

		2011
	Birr	Birr
Opening charges on L/C	14,792,653	14,073,095
Rent	549,054	741,916
Telephone, telegram, telex and fax	5,630,212	5,404,142
Sundries	6,877,701	6,961,886
Gain on disposal of fixed assets	354,639	653,647
Gain on disposal assets held for sale	-	224,840
	28,204,260	28,059,526

Included in sundries income Birr 3,124,952.71 represents old cashier payments order written back as per the Bank's policy.

20 INTEREST EXPENSE

		2011
	Birr	Birr
Savings deposits	194,215,476	159,141,550
Fixed time deposits	14,235,990	4,576,076
	208,451,466	163,717,626

21 GENERAL AND ADMINISTRATION EXPENSES

		2011
	Birr	Birr
Office rent	29,603,326	22,669,601
Depreciation	15,270,207	13,166,847
Postage, telephone, telegram, telex/fax	4,577,097	4,516,838
Stationery and printing	7,815,424	6,161,633
Transportation	6,645,784	5,595,444
Advertisements	3,814,659	3,954,236
Car and representation allowance	1,319,972	1,202,665
Repair and maintenance	3,797,662	2,793,660
Fuel and lubricants	4,584,372	3,334,180
Insurance	3,627,020	2,926,553
Per diems and travel	2,157,391	1,384,744
Correspondent charges	987,213	813,056
SWIFT services	527,764	590,523
Utilities	1,071,498	898,263
Consultancy	-	10,379
Amortization	9,959	9,959
Donations and contributions	120,941	217,200
Annual reception	2,634,465	1,732,305
Bank charges	1,366,735	626,529
Board office expenses	54,000	54,000
Membership and subscriptions	388,665	342,996
Entertainment	978,406	887,707
Inauguration of branches	395,358	575
Legal	54,375	56,448
License fee	8,550	7,550
Cleaning Supplies	444,075	345,338
Wages	638,160	317,093
Transportation of currency	322,676	223,399
Loss on disposal of assets held for sale	23,335	3,043,479
Sundries	2,077,082	1,168,965
	95,316,169	**79,052,165**

22 DIRECTORS' SHARES ON PROFIT

The Board of Directors Remuneration is calculated in compliance with Directive No.SBB/49/2011 which has been issued by National Bank Of Ethiopia, effective from January 15,2011, which limits the maximum compensation of Birr 50,000 for each Board member. The balance has been shown in the profit and loss account.

23 EARNINGS PER SHARE

The rate of earnings per share is the return per share computed on the basis of the net profit after tax divided by the weighted average number of shares held during the year.

24 CONTINGENT LIABILITY AND COMMITMENTS

		2011
	Birr	Birr
Contingent Liability;		
Letter of Guarantee	140,901,145	64,603,373
Letter of Credit	521,119,677	273,155,240
	662,020,822	**337,758,613**

25 MEMORANDUM OF ACCOUNTS

		2011
	Birr	Birr
Stock of traveler cheques	175,853	64,780
OBC-Own branches and other banks' city clearance	49,042,258	76,750,261
IBC-Acceptance and sight	121,169,027	89,867,891
Outward document bills sent for collection - foreign	1,345,291	2,886,251
Interest on non performing loans	63,103,222	63,493,235
Loans and advances written off Kept in memorandum accounts	197,772,673	163,764,613
Money bags	802	5,720
	432,609,126	**396,832,751**

አቢሲንያ ባንክ አ.ማ.
BANK OF ABYSSINIA S.C.

ዓመታዊ ሪፖርት

እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2012
ለተጠናቀቀው በጀት ዓመት

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ማውጫ

አቢሲንያ ባንክ
BANK OF ABYSSINIA

ራዕይ

አቢሲንያ የታላቂቷ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ስያሜ እንደነበረ ሁሉ፣ አቢሲንያ ባንክም በኢትዮጵያ የባንክ ኢንደስትሪ ውስጥ እንደመጀመሪያነቱ አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን እየቀየሰ ዝናውን ጠብቆ በዓለም ምርጥ የተባለውን የባንክ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡

ተልዕኮ

ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን በማቀፍ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየታገዘ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የባንክ አገልግሎቶችን እንዲሠጥ፣ ለአካባቢ ጥበቃም ልዩ ትኩረት በመስጠትና ማህበራዊ ግዴታውንም በአግባቡ በመወጣት ትርፋማነትንና ዕድገትን እያረጋገጠ የሚጓዝ ባንክ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

እሴቶች

ጠንካራ አንድነት፣ ታማኝነት እና ሃቀኝነት፣

ብቃት ያለው የደንበኞች አገልግሎት፣

የዓላማ ፅናት፣

ለዜጎች ዕኩል የሥራ ዕድል መፍጠር፣

የሠራተኞችን ፍላጎት ማርካት፣

የተቀናጀ የህብረት ሥራን መፍጠር፣

መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣

ማህበራዊ ግዴታን በአግባቡ መወጣት፣

አዳዲስ የአሰራር ሥልቶችን መቀየስ፣

ለባለአክስዮኖች ተመጣጣኝ ትርፍ ማስገኘት፡፡

ዋና ዋና ክንውኖች በንጽጽር

(ገንዘብ በሚሊዮን ብር)

	2011/12	2010/11	2009/10	2008/09	2007/08
አጠቃላይ ሀብት	8,239.51	7,296.56	6,279.54	5,476.63	4,269.95
አጠቃላይ የብድር መጠን	3,897.41	3,315.69	3,153.24	2,708.97	2,817.15
አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ	6,771.25	6,075.26	5,138.85	4,494.19	3,477.77
አጠቃላይ ካፒታል	906.59	660.76	585.49	519.23	420.08
አጠቃላይ ገቢ	723.08	618.06	468.94	404.81	347.45
አጠቃላይ ወጪ	434.50	359.68	272.61	259.41	325.54
አጠቃላይ ትርፍ ከግብር በፊት	288.58	258.38	196.34	145.39	21.91
አጠቃላይ ትርፍ ከግብር በኋላ	216.31	180.93	140.58	100.37	16.66
የተጣራ ትርፍ	215.77	178.44	140.58	100.37	16.66
የገንዘብ አስቀማጭ ደንበኞች ብዛት (በቁጥር)	331,831	288,259	263,167	225,660	215,719
የሠራተኞች ብዛት (በቁጥር)	2,105	1,920	1,824	1,721	1,503
የቅርንጫፎች ብዛት (በቁጥር)	63	55	48	46	43

15 ኛው የባለአክስዮኖች ዓመታዊ ጉባዔ ሲካሄድ

የዲሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር መልዕክት

ከሁሉ አስቀድሜ፣ የባንኩን 2011/12 የሥራ አፈፃፀም ለባንኩ ባለአክስዮኖች አጠቃላይ ጉባዔ ስገልፅ የተሰማኝን ደስታ በራሴና በዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ስም ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት፣ ቀድሞ የነበረው ዓለም አቀፉ የገንዘብ ቀውስ መሻሻል ለብዙ የአውሮፓ ሀገሮች አዎንታዊ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም አንዳንድ የክፍለ አህጉሩ አገራት ግን አሁንም በቀውሱ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን የአለም ኢኮኖሚ በአጠቃላይ ሲጤን የምርት እድገት አሳይቷል፡፡

እንደ ዎርልድ ኢኮኖሚክ አውት ሉክ እትም የሚያዚያ 2012 ዘገባ፣ በ2011 ላይ የኒልዮሽ ሲሄድ የነበረው የዓለም ኢኮኖሚ ቀስ በቀስ እያገገመ መጥቷል፡፡ በተለይ በ2011 አጋማሽ ላይ በአሜሪካ የአንዳንድ እንቅስቃሴዎች መሻሻልና በዩሮ ዞን ከኢኮኖሚ ቀውሱ አንፃር ተሻሽለው የወጡ ፖሊሲዎች የዓለም ኢኮኖሚን ክፉኛ ከማሽቆልቆል ሥጋት በመጠኑም ቢሆን እየታደጉት ነው፡፡

በዚህም መሠረት አዝጋሚ የሆነ መሻሻል በዋነኞቹ የበለፀጉ ሀገራት ላይ ታይቷል፡፡ ሪፖርቱ አክሎ እንደጠቆመው ከተተነበየውም በላይ የኢኮኖሚ እድገት እንደሚኖርና የፋይናንስ እንቅስቃሴው በተሻለ ሁኔታ እንደሚቀጥል የሚገልፅ ሲሆን፤ በተጨማሪም፣ የጂኦፖለቲካው ውጥረትም የመርገብ ሁኔታ አሳይቷል፡፡

በ2012 ዓ.ም. በአንዳንድ ሀገራት የገንዘብ አቅም ማደግ ሲታይ፣ በሌሎች ሀገራት ደግሞ የገንዘብ የመግዛት አቅም ወርዶ ታይቷል፡፡ በአጠቃላይ በማደግ ላይ ባሉትና ባደጉት ሀገራት ላይ ለተንፀባረቀው

የኢኮኖሚ እድገት ማዝገም ከዩሮ ዞን ቀውስ ጋር ያልተያያዙ ጉዳዮችም ወሳኝ ሚና ነበራቸው፡፡ ከሰሃራ በታች የሚገኙ ሀገራት የኢኮኖሚ እድገት ግን የሸቀጦች ዋጋ በፈጠረለት ምቹ ሁኔታ እንደከዚህ ቀደሙ እየታገዘ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ነው፡፡

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች የሚይዙትን ዝቅተኛውን የተቀማጭ መጠን ከ15 በመቶ ወደ 10 በመቶ በማውረድና በቀላሉ ወደ ገንዘብ ሊለወጥ የሚችለው የሀብት መጠንን (Liquid Asset) ከተቀማጭ ገንዘብ ጋር ሊኖረው የሚችለውን ጥምረት ከ25 በመቶ ወደ 20 በመቶ በመቀነስ የገንዘብ ፖሊሲውን ማሻሻያ አድርጎበታል፡፡

በተጨማሪም፣ ባንኮች ከሚለቁት ብድር 27 በመቶውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ሰነድ እንዲገዙ የሚያስገድደው አዲሱ የሰነድ ግብይት (Bill Market) መመሪያ በግል ባንኮች የብድር እንቅስቃሴ ላይ ጫና የፈጠረ ሲሆን፣ በተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ ረገድ በባንኮች መካከል ያለውን ውድድር ከፍተኛ አድርጎታል፤ ወደፊትም በዚሁ መልክ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡

በእነዚህ ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ የኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ሆኖ ባንኩ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በበጀት ዓመቱ የሚጠቀሰው አንዱ ትልህ ተግባር ባንኩ አገልግሎቱን ዘመናዊ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም አዳዲስ ደንበኞችን ለመሳብና ነባሮችንም ለማቆየት የሚያስችለው የኮር ባንኪንግ የባንክ አገልግሎት አፈፃፀም ተጠቃሽ ነው፡፡

በተጠናቀቀው የ2011/12 በጀት ዓመት ባንኩ በሁሉም ዘርፎች አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ ለምሳሌ የባንኩን ያልተጣራ ትርፍ ስንመለከት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ11.5 በመቶ ልዩነት በማሳየት ብር 288.58 ሚሊዮን ሆኖ ሲመዘገብ የተቀማጭ ገንዘብ መጠንም 6.7 ቢሊዮን በመድረስ የ11.5 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ የብድር መጠናችንም 3.9 ቢሊዮን ላይ የደረሰ ሲሆን፣ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ17.5 በመቶ ብልጫ አሳይቷል፡፡

ሌላው ተጠቃሽ ተግባር የአሠራር ለውጥን ለማምጣት በባንኩ የሥራ ክፍሎች እገዛ የተሰራው ሥራም ውጤታማ መሆኑ ነው፡፡ በተለይ የሥራ ሂደትን በመከለስ፣ ፖሊሲዎችንና የአፈፃፀም ሂደቶችን በመለየትና የአንድ መስኮት የባንክ አገልግሎትን በቅርንጫፎች ላይ ተግባራዊ በማድረግ የተሰሩት ተግባራት ደንበኞች በብቃትና በፍጥነት አገልግሎት እንዲያገኙ አስችለዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ የአጠራጣሪ ብድሮችን ምጣኔ (NPL) ለመቀነስ በተደረገው ጥረት ባንኩ ውጤታማ የነበረ ሲሆን፣ በተቆጣጣሪው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከወጣው ዝቅተኛው መስፈርትም አኳያ ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞም፣ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትና ከፍተኛ የሥራ አመራሩ የባንኩን አጠቃላይ ቀጣይ ሂደቶችን ለመገምገም በየጊዜው ውይይት እያደረጉ ነው፡፡

በአጠቃላይ በ2011/12 ለባንኩ የሥራ አፈፃፀም የባንኩ ባለድርሻ አካላት ላደረጉልን ማበረታቻ፣ ውድ ደንበኞቻችን በባንካችን ላይ ላሳዩት ሙሉ እምነት እንዲሁም የባንኩ የሥራ አመራር አካላትና ሠራተኞች በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለባንኩ እድገት ላደረጉት አስተዋጽኦ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም፣ በበጀት ዘመኑ የሥራ ባልደረቦቼ የሆኑትን የዲሮክተሮች ቦርድ አባላት በአንድነት መንፈስ ለነበራቸው የሥራ መነሳሳትና ቁርጠኝነት ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

አመሰግናለሁ!

መሐሪ ዓለማየሁ

የባንኩ ኘሬዝዳንት መልዕክት

በ2011/12 በጀት ዓመት፣ አቢሲንያ ባንክ ገበያውን ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶችን ያደረገ ሲሆን፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ብቃትን ማዕከል ባደረገ መልኩ ምርጥ የተሰኘውን የባንክ አገልግሎት ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል፡፡ በተጨማሪም፣ ወሳኝ የሚባሉት ሁሉም የባንኩ የሥራ አፈፃፀሞች ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀሩ እድገታቸው ቀጥሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የባንኩ አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ ካለፈው በጀት ዓመት አኳያ የ696 ሚሊዮን ብር ብልጫ ያስመዘገበ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ ማብቂያ ላይ ብር 6.77 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በተመሳሳይም የብድር መጠናችን በ582 ሚሊዮን ብር ያደገ ሲሆን፣ ይኸውም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ 3.90 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡

የባንኩን አጠቃላይ ገቢን ስንመለከትም ባንኩ በበጀት ዘመኑ ብር 723 ሚሊዮን አጠቃላይ ገቢ ያገኘ ሲሆን፣ ይኸውም ዓምና ከነበረው የብር 618 ሚሊዮን ገቢ ጋር ሲነፃፀር የብር 105 ሚሊዮን ወይም የ17 በመቶ ብልጫ አሳይቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ የባንኩ አጠቃላይ ወጪ ብር 435 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን፣ ይኸውም በ2011/12 በጀት ዓመት አጠራጣሪ ለሆኑ ብድሮች መጠባበቂያ የተያዘውንም ገንዘብ ያካትታል፡፡ በዚህም መሠረት ባንኩ

ከታክስ በፊት ያሳየው አጠቃላይ ትርፍ ብር 288.58 ሚሊዮን ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ የሚመለከታቸው የባንኩ የሥራ ክፍሎች ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረትም የባንኩ የሀብት ጥራት የተሻሻለ ከመሆኑም በላይ፣ ምጣኔውን ወደ ነጠላ አሀዝ በማውረድ የሀብት ጥራታችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው መስፈርትም በታች እንዲሆን ለማድረግ ተችሏል፡፡

በሌላም በኩል፣ የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድና የሥራ አመራሩ ዋነኛ አጀንዳ የሆኑት የኮር ባንኪንግ የባንክ አገልግሎት ትግበራ፣ የመረጃ ማዕከል ግንባታና ተዛማጅ ሥራዎች በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚደረጉ ላረጋግጥ እወዳለሁ፡፡

በበጀት ዓመቱ ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት መካከል ባንኩ አገልግሎት አሰጣጡን ማዕከል አድርጎ ያከናወነው የሥራ ሂደት ፍተሻ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህም የባንኩን የአገልግሎት አሠጣጥ መሠረታዊ በሆነ መልኩ በመለወጥ የሚያሻሽል ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል፣ በበጀት ዓመቱ ትኩረት ከተቸራቸው ቁልፍ ተግባራት መካከል የባንኩን ገፅታ በመገንባት ረገድ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርገው የባንኩ የዋና መ/ቤት ሕንፃ ግንባታ ቅድመ ዝግጅት ይገኝበታል፡፡

በዚህ አጋጣሚ የባንኩ የሥራ አመራር ለውድ ደንበኞቹ የሚሰጠውን አገልግሎት ከመቼውም ጊዜ በላይ እንደሚያሻሽል እየገለጽኩ፣ በቀጣይ ዓመታትም ባንኩ ዓለም አቀፍና ደረጃውን የጠበቀ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት ያነገበውን ራዕይ ለማሳካት ያለውን ቁርጠኝነት ላረጋግጥ እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም፣ በበጀት ዓመቱ ባንኩ ላከናወናቸው ተግባራት የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ ውድ ደንበኞቻችንን፣ የባንኩ ባለአክስዮኖችንና ሠራተኞችን በአጠቃላይም የባንኩን ባለድርሻ አካላት ሁሉ ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በቀጣይ ባንኩ ውጤታማነቱን ጠብቆና አጠናክሮ ለመሄድ እንዲችል ድጋፋቸው እንደማይለየን እምነቴ ነው፡፡

አመሰግናለሁ

አዲሱ ሃባ

የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ፣ ሰኔ 30 ቀን 2012 ለተጠናቀቀው በጀት ዓመት ኦዲት የተደረገው የባንኩን የሒሳብ መግለጫዎች ለባንኩ ባለአክስዮኖች አጠቃላይ ጉባዔ ያቀርባል፡፡

የኦዲተሮች ሪፖርትም የሀብትና ዕዳ መግለጫ፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ የገንዘብ ፍሰት መግለጫንና የሂሳብ መግለጫዎች ማብራሪያዎችን ያካተተ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ዋና ዋና ክንውኖች በዚህ ሪፖርት ውስጥ ጠቅለል ብለው ቀርበዋል፡፡

1. የሥራ አፈፃፀም

1.1 ተቀማጭ ገንዘብ

በ2011/12 የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የባንኩ አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ መጠን ብር 6.77 ቢሊዮን ሲደርስ፣ ይኸውም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ695.99 ሚሊዮን ብር ወይም 11.5 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ለዚህም በቁጠባ ሒሳብ የተቀመጠው ገንዘብ በብር 500.85 ሚሊዮን ወይም 11.3 በመቶ እንዲሁም በተንቀሳቃሽ ሒሳብ የተቀመጠው ገንዘብ በብር 39.13 ሚሊዮን ወይም የ2.5 በመቶ እንዲሁም በጊዜ ገደብ የተቀመጠው የገንዘብ መጠን በብር 156.01 ሚሊዮን ወይም 265 በመቶ እድገት አስመዝግበዋል፡፡ ከአስቀማጮች ጋር በተያያዘም ባለፈው ዓመት የነበረው 288,259 የአስቀማጮች ቁጥር ወደ 331,831 አድጓል፡፡

አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ

(በሺህ ብር)

የተቀማጭ ገንዘብ በዓይነት	2011/12		2010/11		ዕድገት	
	ገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	በቁጥር	በመቶኛ
በተንቀሳቃሽ ሒሳብ የተቀመጠ	1,630,502	24	1,591,370	26	39,132	2.5
በቁጠባ ሒሳብ የተቀመጠ	4,923,709	73	4,422,862	73	500,847	11.3
በጊዜ ገደብ የተቀመጠ ገንዘብ	217,035	3	61,027	1	156,008	255.6
ድምር	**6,771,246**	**100**	**6,075,259**	**100**	**695,987**	**11.5**





1.2 ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች

በ2011/12 በጀት ዓመት የባንኩ የብድርና ቅድሚያ ክፍያዎች መጠን ወደ ብር 3.90 ቢሊዮን አድጓል። ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር 581.72 ሚሊዮን ወይም 17.5 በመቶ እድገት አሳይቷል። በጊዜ ገደብ የተሰጠው ብድር በብር 518.52 ሚሊዮን ወይም 20.3 በመቶ ማደጉ የአጠቃላይ ብድርና ቅድሚያ ክፍያዎችን ዕድገት ከፍ እንዲል አድርጓል።

ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች በዓይነት

(በሺህ ብር)

የብድር ዓይነት	2011/12		2010/11		ዕድገት	
	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	በቁጥር	በመቶኛ
በጊዜ ገደብ የተሰጡ ብድሮች	3,085,480	79	2,555,741	77	529,739	20.7
ኦቨር ድራፍት	721,496	19	700,143	21	21,353	3.0
ቅድሚያ ክፍያዎች	90,431	2	59,804	2	30,627	51.2
ድምር	**3,897,407**	**100**	**3,315,688**	**100**	**162,618**	**17.5**



የብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች ድርሻ



በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎችን ሥርጭት ስንመለከት፣ የሀገር ውስጥ ንግድ 43 በመቶውን በመያዝ የአንበሳውን ድርሻ ሲይዝ፣ የወጪ ንግዱ ደግሞ 16 በመቶውን በመያዝ ሁለተኛ ደረጃን ይዟል፣ የግንባታና የገቢ ንግዱ ደግሞ እኩል 14 በመቶውን በመያዝ ይከተላሉ።

ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች በክፍለ ኢኮኖሚ

(በሺህ ብር)

ክፍለ - ኢኮኖሚ	2011/12		2010/11		ዕድገት	
	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	በቁጥር	ድርሻ (በመቶኛ)
የአገር ውስጥ ንግድና አገልግሎት	1,689,161	43	1,145,674	35	543,487	47.4
ትራንስፖርት	86,924	2	115,793	3	(28,869)	(24.9)
የገቢ ንግድ	526,436	14	459,900	14	66,535	14.5
ኢንዱስትሪ	235,928	6	307,760	9	(71,832)	(23.3)
ግንባታ	528,919	14	527,483	16	1,436	0.3
የወጪ ንግድ	606,496	16	508,125	15	98,371	19.4
ግብርና	4,350	0	5,349	0	(999)	(18.7)
በሸቀጣሸቀጦች መያዣነት	106,609	3	137,392	4	(30,783)	(22.4)
*ወደ ሕግ መምሪያ የተላለፉ ብድሮች	40,029	1	67,032	2	(27,003)	(40.3)
የግለሰብ	72,554	2	41,179	1	31,375	76.2
ድምር	**3,897,406**	**100**	**3,315,688**	**100**	**581,718**	**17.5**

* ወደ ሕግ መምሪያ የተላለፉ ብድሮች በተለያዩ ክፍለ-ኢኮኖሚዎች የሚገኙ ናቸው።

ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች በክፍለ-ኢኮኖሚ



1.3 የዓለም አቀፍ ባንክ አገልግሎት የሥራ አፈፃፀም

በተጠናቀቀው የ2011/12 በጀት ዓመት ባንኩ በዓለም አቀፍ ባንኮች አገልግሎት በኩል ያገኘው ገቢ ብር 168.58 ሚሊዮን ደርሷል። ይኸውም ገቢ ከአጠቃላይ የበጀት ዓመቱ ገቢ 22 በመቶውን የሚይዝ ነው።

በሌላም በኩል፣ ባንኩ በበጀት ዓመቱ ብር 3,266.2 ሚሊዮን የሚደርስ የውጭ ምንዛሬ የሰበሰበ ሲሆን፣ ይኸውም ከሐዋላ፣ ከገቢና ከወጪ ንግድ እንዲሁም ከቼክ አገልግሎት የተገኘ ነው።
ይኸውም ገቢ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በብር 64.6 ሚሊዮን ወይም 2 በመቶ አድጓል።

አቢሲንያ ባንክ የብድር አገልገሎት ከሚሰጣቸው ተቋማት በከፊል

ታረቅ ሳቢት ኃ.የተ.የግል ማህበር-ሆቴል

ጀማል አብዶ እና ሳህሌ ል.ጋ.- ኮንስትራክሽን

ይርጋ ጨፌ ቡና ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን

መሠረት ዱቄት ፋብሪካ ኃ.የተ.የግል ማህበር



ለግዠሪ ኤንድ ፖፒዩላር ትሬዲንግ - አስመጪ

2 ገንዘብ ነክ ክንውን

2.1 ገቢ

በተጠናቀቀው የ2011/12 የበጀት ዓመት ባንኩ 723.08 ሚሊዮን አጠቃላይ ገቢ ያገኘ ሲሆን፣ ይኸውም ገቢ ባንኩ እስከአሁን ካገኘው ገቢ ትልቁን ቦታ የሚይዝ ከመሆኑም በላይ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ17 በመቶ ወይም በብር 105 ሚሊዮን ብልጫ አሳይቷል፡ ፡ ለበጀት ዓመቱ የገቢ እድገትም በወለድ ገቢ፣ በአገልግሎት ክፍያ፣ በኮሚሽን ገቢ እና በሌሎችም ገቢዎች የተመዘገበው ውጤት ለአጠቃላይ ገቢው ማደግ ምክንያት ነው፡፡

ገቢ በዋና ዋና የገቢ ዓይነቶች

(በሺህ ብር)

የገቢው ዓይነት	2011/12		2010/11		ዕድገት	
	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	በቁጥር	በመቶኛ
የወለድ ገቢ	497,528	69	372,079	60	125,449	33.7
የኮሚሽን ገቢ	25,735	4	22,575	4	3,160	14.0
ከውጭ ምንዛሬ ተመን ለውጥ የተገኘ ገቢ	85,593	12	128,746	21	(43,365)	(33.7)
ከውጭና ከሀገር ውስጥ የአገልግሎት ክፍያዎች የተገኘ ገቢ	86,274	12	66,602	11	19,672	29.5
ሌሎች ገቢዎች	28,204	4	28,060	4	144	0.15
ከተበላሹ ብድሮች መጠባበቂያ ተመላሽ	-	-	-	-	-	-
ያለፈው ዓመት ማስተካከያ	(23)	-	-	-	-	-
ድምር	**723,081**	**100**	**618,062**	**100**	**105,019**	**17**



2.2 ወጪ

ባንኩ በ2011/12 አጠራጣሪ ለሆኑ ብድሮች የተያዘውን መጠባበቂያ ጨምሮ ያወጣው አጠቃላይ ወጪ ብር 435 ሚሊዮን ነው፡፡ ይኸውም ወጪ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር 75 ሚሊዮን ወይም የ20.8 በመቶ ዕድገት ያሳየ ሲሆን፣ በተቀማጭ ሒሳቦች ላይ የተከፈለ ወለድ፣ አጠቃላይ ወጪ፣ ለአጠራጣሪ ብድሮች የተያዘው መጠባበቂያ፣ የሥራ ማስኬጃና የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንደ ቅደም ተከተላቸው በበጀት ዓመቱ ለታየው የወጪ ዕድገት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

ወጪ በዋና ዋና የወጪ ዓይነቶች

(በሺ.ህ ብር)

የወጪ ዓይነቶች	2011/12		2010/11		ዕድገት	
	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	በቁጥር	በመቶኛ
በተቀማጭ ሒሳቦች ላይ የተከፈለ ወለድ	208,451	48	163,718	46	44,733	27.3
ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም	106,292	24	90,806	25	15,486	17.1
የሥራ ማስኬጃ	95,619	22	79,419	22	16,200	20.4
አጠራጣሪ ለሆኑ ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች	23,629	5	18,997	5	4,632	24
ለሌሎች ተሰብሳቢዎች መጠባበቂያ	511	0	6,739	2	(6,228)	(92)
ድምር	**434,502**	**100**	**359,679**	**100**	**74,823**	**20.80**



2.3 ትርፍ

በ2011/12 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ለብድሮች መጠባበቂያ ብር 23.63 ሚሊዮን ከተያዘ በኋላ የባንኩ አጠቃላይ ትርፍ ብር 288.58 ሚሊዮን ሲሆን፣ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር 30.2 ሚሊዮን ወይም የ11.7 በመቶ ብልጫ አሳይቷል። በተጨማሪም፣ የባንኩ አጠቃላይ ትርፍ ከግብር በኋላ የብር 37.3 ሚሊዮን ወይም የ15 በመቶ ብልጫ በማሳየት ብር 216 ሚሊዮን ሲደርስ፣ ሌሎች አስፈላጊ ተቀናሾች ከተደረጉ በኋላ ደግሞ የተጣራ ትርፉ ብር 215.77 ሚሊዮን ደርሷል። ለትርፉ ማደግ የሀብት ጥራትንና የሥራ አፈፃፀም ውጤትን ለማሻሻል የተደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ትርፍ ከግብር በፊት

(በሺ.ህ ብር)

ዝርዝር	2011/12	2010/11	ዕድገት	
			በቁጥር	በመቶኛ
አጠቃላይ ገቢ	723,415	618,062	105,019	17.0
ጠቅላላ ወጪ	434,502	359,679	74,823	20.8
ከግብር በፊት የተገኘ ትርፍ	**288,579**	**258,383**	**30,196**	**11.7**



2.4 የባንኩ ካፒታል

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የባንኩ ካፒታል ብር 906.59 ሚሊዮን ደርሷል። ይህ የገንዘብ መጠን ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር 246 ሚሊዮን ጭማሪ አሳይቷል። በበጀት ዓመቱ የተከፈለ ካፒታል 52 በመቶ፣ ሕጋዊ መጠባበቂያ 29 በመቶ እና ያልተከፋፈለ የትርፍ መጠን 21 በመቶ እድገት አስመዝግበዋል።

የባንኩ ካፒታል

(በሺ ብር)

የካፒታል አይነቶች	2011/12		2010/11		ዕድገት	
	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	የገንዘብ መጠን	ድርሻ (በመቶኛ)	በቁጥር	በመቶኛ
የተከፈለ ካፒታል	478,898	53	315,000	48	163,898	52
ከአክስዮን ሽያጭ ከዋጋ ብልጫ የተሠበሰበ	2,828	-	2,828	-	-	-
ሕጋዊ መጠባበቂያ	237,552	26	183,610	28	53,942	29
ልዩ መጠባበቂያ	25,919	3	25,919	4	-	-
ያልተከፋፈለ ትርፍ	161,398	18	133,403	20	27,995	21
ድምር	**906,592**	**100**	**660,759**	**100**	**245,836**	**37**

2.5 ጥሬ ገንዘብና በአጭር ጊዜ ወደጥሬ ገንዘብ መቀየር የሚችል ሀብት ፍሰት (Liquidity)

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የባንኩ ጥሬ ገንዘብና በፍጥነት ወደ ጥሬ ገንዘብ መለወጥ የሚችል ሀብት (liquid asset) ከባንኩ የተጣራ የአጭር ጊዜ ተከፋይ (net current liability) ጋር ሲነፃፀር 36.23 በመቶ የመሸፈን አቅም አለው። በሌላም በኩል፣ በበጀት ዓመቱ የባንኩ ካፒታል ለአደጋ ሊጋለጥ ከሚችል ሀብት ጋር ያለው ጥመርታ (capital to risk weighted assets) 15.63 በመቶ ሲሆን፣ ይኸውም ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካወጣው 8 በመቶ ዝቅተኛ መስፈርት በላይ ሆኖ ይታያል።

3 አስተዳደራዊና ሌሎች ጉዳዮች

3.1 የሰው ኃይል

በ2011/12 በጀት ዓመት ማብቂያ ላይ የባንኩ አጠቃላይ ሠራተኞች ቁጥር 2,105 ሲደርስ፣ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ቁጥሩ በ185 ሠራተኞች ጨምሯል።

በበጀት ዓመቱ ባንኩ ክሰው ኃይል ልማት አኳያ፣ በተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተለያዩ ደረጃዎች እየተማሩ ለሚገኙ 398 ሠራተኞች የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

እየተተገበረ ካለው የኮር ባንኪንግ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ 592 ለሚሆኑ ሠራተኞች የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ 400 ያህሉ T-24 የተሰኘውን የኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ ኘሮጀክት አፈፃፀም፣ የሀገር ውስጥ የባንክ አገልግሎትና የብድር አገልግሎት ላይ ስልጠና ወስደዋል።

የሠራተኞች በዓል ቀን ሲከበር

3.2 የቅርንጫፍ መስፋፋት

በተጠናቀቀው የ2011/12 በጀት ዓመት ባንኩ ተጨማሪ ስምንት አዳዲስ ቅርንጫፎችን በመክፈት የቅርንጫፎቹን ቁጥር ወደ 63 አሳድጓል:: ከተከፈቱት ቅርንጫፎች አራቱ ቸርችል፣ ሳር ቤት፣ ሲ. ኤም. ሲ.እና ካዛንቺስ ቅርንጫፎች በአዲስ አበባ የተከፈቱ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ አራቱ ጨሮ፣ ታቦር፣ ወላይታ ሶዶና ፍኖተ ሰላም ቅርንጫፎች ደግሞ በክልል ከተሞች የተከፈቱ ናቸው::

ባንኩ በቀጣይም ለባንክ ሥራ አዋጪ በሆኑ በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ቅርንጫፎቹን ማስፋፋት ይቀጥላል::

ካዛንችስ ቅርንጫፍ

ሣርቤት ቅርንጫፍ

ፍኖተ ሰላም ቅርንጫፍ

ጭሮ ቅርንጫፍ

ታቦር ቅርንጫፍ

ወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ

ቸርችል ጎዳና ቅርንጫፍ

ሲ.ኤም.ሲ ቅርንጫፍ

3.3 የገበያ ዕድገት

ከገበያ ዕድገት ጋር ተያይዞ ባንኩ በበጀት ዓመቱ በደሴ፣ ጎንደር፣ ባሕር ዳርና ደብረ ብርሃን ቅርንጫፎች የደንበኞች ቀን በዓልን ያዘጋጀ ሲሆን፣ የዝግጅቶቹ ዓላማም ከባንኩ ጋር እየሠሩ ላሉ ደንበኞች ምሥጋና ለማቅረብና ከደንበኞች ጋር ገንቢ ውይይት በማካሄድ በአገልግሎት አሰጣጥና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች አንፃር ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ተግባራት ለማሻሻል እንዲሁም ባንኩ ከደንበኞቹ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ነው፡፡ በተጨማሪም፣ በጪሮ፣ በአዳማ መናኸሪያ፣ በአዲ ሓቂ፣ በፍኖተሰላም፣ በወላይታ ሶዶና በታቦር ቅርንጫፎች የቅርንጫፍ ምረቃ በዓል ተካሂዷል፡፡ በዚህም የባንኩን አገልግሎት ለማስተዋወቅ የተቻለ ሲሆን፣ አዳዲስ ደንበኞችን ለማግኘት ተችሏል፡፡

የውጭ ምንዛሬ አሰባሰብንና ዓለም አቀፍ የባንክ አገልግሎትን ከማሳደግ አኳያም ባንኩ ገበያ የማግኘት እንቅስቃሴውን የቀጠለ ሲሆን፣ ከዚሁም ጋር ተያይዞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ከሆኑ የገንዘብ አስተላላፊ ተቋማት ጋር የሥራ ግንኙነት ለማድረግ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

በሌላም በኩል፣ የቅርንጫፎች የሥራ ሰዓት እንዲያድግ የተደረገ ሲሆን፣ የባንኩን ገፅታ ከመገንባት አኳያም በተለያዩ ስልቶች ባንኩን ለማስተዋወቅና ገፅታውን ይበልጥ ለመገንባት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

3.4 የመረጃ ኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂ

በ2011/12 በጀት ዓመት የባንክ ሥርዓት ፕሮጀክት ትግበራ (BSIP) ዘመናዊ የባንክ ቴክኖሎጂን አሁን በተያዘው በጀት ዓመት ሁለተኛው ሩብ ዓመት ላይ ሙሉ ለሙሉ ለመተግበር በሚያስችል መልኩ ከጫፍ ደርሷል፡፡ ከዚሁ አንፃር እንደ ኮር ባንኪንግ ስርዓት ትግበራ፣ የመረጃ ማዕከል ግንባታ እንዲሁም ተያያዥ የባንክ አገልግሎት ዝግጅት እየተጠናቀቀ ነው፡፡ በተጨማሪም ባንኩ የአንድ መስኮት አገልግሎትን በ15 ቅርንጫፎቹ ለውድ ደንበኞቹ እየሠጠ ሲሆን፣ ይኸው አገልግሎት በጥቂት ጊዜያትም በሁሉም ቅርንጫፎች ይዳረሳል፡፡ ይህ የአንድ መስኮት የባንክ አገልግሎትና የተራ አጠባበቅ ሥርዓት ሥራ መጀመር ደንበኞች አጭር በሆነ ጊዜ አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

ከዘመናዊ የባንክ ቴክኖሎጂው ጋር በተያያዘ ከሥራ ሂደት ለውጥ አኳያ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች በርካታ ሥልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን፣ የተለያዩ ተግባራትም ተከናውነዋል፡፡

በ2012/13 በጀት ዓመት ሁለተኛው ሩብ ዓመት ላይ ሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች በአዲሱ ስርዓት ይገናኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

4. የባንኩ ቀጣይ ዕቅድ

ባንኩ በተከለሰው ሦስተኛው ዙር የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ መሠረት የ2012/13 ዓመታዊ ዕቅድን አዘጋጅቷል፡፡ ዓመታዊ ዕቅዱ ባንኩ ባስቀመጣቸው ስምንት ዋና ዋና ቁልፍ ተግባራት ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ እነዚህም የገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም፣ የሰው ኃይል አስተዳደር፣ ደንበኛ ተኮር አገልግሎት፣ ገበያ፣ የመረጃ ኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት፣ መልካም አስተዳደር፣ የሀብት ጥራትና የመገልገያ መሣሪያዎች ግንባታ ናቸው፡፡

ከመረጃ ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ተያይዞ ከገበያ ድርሻ አንጻርና ከፖሊሲዎች መለዋወጥ አኳያ ባንኩ በሁሉም ዘርፎች አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ የሚችል አቅጣጫ ለማስያዝ የባንኩን የወደፊት ስልታዊ አካሄድ በማጤን ላይ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሠረት በ2012/13 በጀት ዓመት ባንኩ በሁሉም ቅርንጫፎቹ የኮር ባንኪንግ የባንክ አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን፣ የካርድ ባንኪንግ አገልግሎትንም መስጠት ይጀምራል፡፡

የባንኩን ገፅታ ከመገንባት አኳያ ከፍተኛ ሚና የሚኖረው የዋና መ/ቤት ሕንፃ ግንባታም በበጀት ዓመቱ ትኩረት የተቸረው ነው፡፡

ከባንክ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ባንኩ የሀብት ጥራት፣ ቀጣይ እድገትና ትርፋማነትን መሠረት ባደረገ መልኩ አዳዲስ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅና ቅርንጫፎች በማስፋፋት ረገድ ልዩ ትኩረት በመስጠት ይንቀሳቀሳል፡፡

5. ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ የቀረበ የውሳኔ ሐሳብ

በ2011/12 በጀት ዓመት ባንኩ ከአጠቃላይ ትርፉ አስፈላጊውን ማቀናነስ ካደረገ በኋላ ብር 215.77 ሚሊዮን የተጣራ ትርፍ አግኝቷል፡፡

በመሆኑም፣ ለሕጋዊ መጠባበቂያ ብር 53.94 ሚሊዮን፣ እንዲሁም ለዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚሰጠው የትርፍ ድርሻ ብር 427.87 ሺህ ከተቀነሰ በኋላ፣ ብር 161.39 ሚሊዮን የባንኩ ባለአክስዮኖች ባላቸው የተከፈለ የአክስዮን ድርሻ መጠን መሠረት እንዲከፋፈል የዲሬክተሮች ቦርድ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡

6. ምሥጋና

የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድና የበላይ አመራሩ ባንኩ ላስመዘገበው ውጤት ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን ለሰጡን የባንኩ ውድ ደንበኞች፣ ባለአክስዮኖችና ሠራተኞች እንዲሁም ለተቆጣጣሪው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምሥጋና ያቀርባሉ፡፡

የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት

1. አቶ መሐሪ ዓለማየሁ ....የቦርድ ሊቀመንበር
2. አቶ አንዱዓለም ደምሳቸው ....አባል
3. ኢንጅነር አወቀ ወንድሜነህ.............................አባል
4. ፕሮፌሰር አየነው እጅጉ ....አባል
5. አቶ ዳኛቸው መሐሪ......................................አባል
6. አቶ ሀብቴ ወልደኪሮስ ....አባል
7. ወ/ሮ ሰብለ ወንጌል ተክሉ................................አባል
8. ዶ/ር ሰሎሞን ባርናባስ...................................አባል
9. አቶ ተዘራ ወዳጆ..አባል

....

መሐሪ ዓለማየሁ
የዳሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር

....

አዲሱ ሐባ
ፕሬዚደንት

AUDITOR'S REPORT

ደገፋ ለሜሣ የኦዲት አገልግሎት
ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት
የሽርክና ማኅበር
የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች
Tel: +251-011-466 11 57 Mobile +251-091-122 32 10
Fax: +251-011-466 15 36 +251-091-198 35 72
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

Degefa Lemessa Authorized Auditors
Limited Partnership
Chartered Certified
Accountants
P.O. Box: 8118
E-mail: deg.lem@ethionet.et
Addis Ababa, Ethiopia

ለአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር ባለአክስዮኖች

ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላበቃው ዓመት በተዘጋጁት የባንኩ

የሂሣብ መግለጫዎች ላይ የቀረበ የውጪ ኦዲተሮች ሪፖርት

1. ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡትን የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ.ም. ላበቃው ዓመት የተዘጋጁትን የሂሣብ መግለጫዎች መርምረናል:: የሂሣብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዲሬክተሮች ቦርድ ሲሆን የእኛ ኃላፊነት በተዘጋጁት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ ባደረግነው ምርመራ ላይ ተመስርተን ገለልተኛ የሆነ የሙያ አስተያየታችንን ለእናንተ መስጠት ነው::

2. ምርመራችንን ያከናወንነው በአጠቃላይ ተቀባይነት ባገኙት የሂሣብ ምርመራ ደንቦች መሠረት ሲሆን ፤ ደንቦቹም፤ ለምርመራ የሚቀርቡትን የሂሣብ መግለጫዎችን ትክክለኛነት የሚያፋልሱ ስህተቶች የሌሉ መሆኑን በአጥጋቢ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ስልት እንዲቀየስና የምርመራ ሥራዎች እንዲከናወኑ ያዛሉ:: የሂሣብ ምርመራ ሥራ የሂሣብ መግለጫዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱና እንደአግባቡ በተመረጡ ሂሣቦችና ደጋፊ ሰነዶቻቸው ላይ ዝርዝር ምርመራ ማከናወንንና ሂሣቦች በመግለጫዎች ውስጥ የተመለከቱበትን ሥፍራና አገላለጥ ትክክለኛነትንና አግባብነትን ማገናዘብ ያካትታል:: በተጨማሪም የምርመራ ሥራ ተመርማሪው የሚከተላቸውን የሂሣብ መርሆዎችን፤ ሂሣብ መግለጫዎቹን ሲያዘጋጅ የሚያደርጋቸውን ጉልህ ግምቶችን፤ የመግለጫዎቹን ይዘትና አቀራረብ ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን መመዘንን ይጨምራል::

3. በኛ አስተያየት፤ ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡት የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች፤ ተቀባይነት ባላቸው የሂሣብ መርሆዎች ላይ በመመስረት የተዘጋጁ ሲሆኑ፤ በአጠቃላይ የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር በሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. የነበረውን ሀብትና ዕዳ፤ በዚያው ዕለት ላለቀው ዓመት ያገኘውን ትርፍና በዓመቱ የነበረውን የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ያሳያሉ::

4. የዲሬክተሮች ቦርድ የሂሣብ መግለጫዎቹን አስመልክቶ በሰጠው ሪፖርት ላይ የምንሰጠው የልዩነት አስተያየት ስለሌለን በ1952 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ሕግ አንቀጽ 374 መሠረት የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የሂሣብ መግለጫዎቹን እንዲያፀድቃቸው ሃሣብ እናቀርባለን::

ደገፋ ለሜሣና ኩባንያው
የተመሰከረላቸው የሂሣብ አዋቂዎች /ለንደን/
የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች

አዲስ አበባ
የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር ኦዲተሮች

መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ. ም.

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የሀብትና ዕዳ መግለጫ
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም.

	ማብራሪያ	ብር	ብር	2003 ብር
ሀብት				
በእጅና በሌሎች ባንኮች ያለ ገንዘብ፣				
በእጅ			811,933,530	792,519,415
በሀገር ውስጥ ባንኮች			12,613,029	193,720,512
በውጭ ሀገር ባንኮች	2ረ		812,485,351	587,059,378
በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያለ የመጠባበቂያ ሂሣብ			650,017,347	835,017,347
በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሉ ሌሎች ሂሣቦች			236,063,468	487,592,111
			2,523,112,726	2,895,908,763
ከሌሎች ባንኮች በመሰብሰብ ላይ ያለ		138,761,208		133,181,515
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰነድ ግዢ	2ተ	1,461,233,000		816,603,000
ኢንቨስትመንት - ኢትዮ ስዊች አ.ማ.	2ቸ	1,258,000		
ተቀማጭና ቅድሚያ ክፍያዎች	3	42,487,663		32,637,861
ለደንበኞች የተሠጡ ብድሮች	2ሐ, 4	3,797,305,660		3,205,208,290
			5,441,045,530	4,187,630,666
ሌላ ሀብት	5ሽ	111,079,216		80,099,712
የወደፊት ወጪዎች	2ሰ 6	68,260,791		27,379,681
ለመሬት ይዞታ	2ሸ 7	458,099		468,058
ቋሚ ሀብት	2መ, 8	95,557,299		86,080,480
			275,355,405	194,027,931
የሀብት ድምር			8,239,513,662	7,277,567,360
ዕዳዎች				
የደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ፣	9			
በተንቀሳቃሽ ሂሣብ		1,630,501,927		1,591,369,708
በቁጠባ ሂሣብ	9	4,923,709,126		4,422,862,487
በጊዜ ገደብ በተቀመጠ ሂሣብ	9	217,034,535		61,026,703
			6,771,245,588	6,075,258,898
ለመተማመኛ የዱቤ ሠነዶች ቅድሚያ ክፍያ		171,110,497		102,765,769
ሌሎች ዕዳዎች	10	315,281,331		358,880,162
የትርፍ ግብር መጠባበቂያ	11	72,248,409		77,416,190
			558,640,237	539,062,121
ወደፊት የሚከፈል የትርፍ ግብር ዕዳ	11.2		3,033,950	2,487,832
የዕዳዎች ድምር			7,332,919,774	6,616,808,851
ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሣቦች				
የተከፈለ ካፒታል	12		478,897,703	315,000,000
በአክሲዮን ሽያጭ ዋጋ ብልጫ የተሰበሰበ			2,827,540	2,827,540
ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ	13		237,551,614	183,609,594
ልዩ የመጠባበቂያ ሂሣብ	14		25,918,839	25,918,839
ያልተከፋፈለ ትርፍ			161,398,192	133,402,537
			906,593,888	660,758,510
የዕዳዎችና የባለአክሲዮኖች ገንዘብ ድምር			8,239,513,662	7,277,567,360

መሐሪ ዓለማየሁ
የዲሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር

አዲሱ ሐባ
ፕሬዝደንት

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የትርፍና ኪሣራ መግለጫ
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

	ማብራሪያ	ብር	ብር	2002 ብር
ገቢ				
ከወለድ	2ሠ,በ, 16		497,487,397	372,078,977
ሲቀነስ፡- የወለድ ወጪ	20		208,451,466	163,717,626
የተጣራ የወለድ ገቢ			289,035,930	208,361,351
ከውጪ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን ለውጥ የተገኘ ትርፍ	17		85,381,411	128,745,904
ከአገልግሎት - ለውጪ ሀገርና ለሀገር ውስጥ	18		86,274,120	66,601,865
ከኮሚሽን	19		25,735,342	22,575,310
ከልዩ ልዩ			28,204,260	28,059,526
			514,631,065	454,343,956
ወጪዎች				
ለሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች		106,291,912		90,805,500
ለአስተዳደርና ለሌሎች	21	95,316,169		79,052,165
ለዲሬክተሮች ቦርድ አበል		195,099		247,161
ለኦዲተሮች አበል		108,000		119,591
ለደንበኞች ለተሰጡ አጠራጣሪ ብድሮች መጠባበቂያ		23,629,459		18,996,907
ለሌሎች አጠራጣሪ ተሰብሳቢዎች መጠባበቂያ		511,353		6,739,377
			226,051,992	195,960,701
ትርፍ - ከትርፍ ግብር መጠባበቂያ በፊት			288,579,072	258,383,255
ሲቀነስ፡ የትርፍ ግብር መጠባበቂያ	11		(72,264,872)	(77,455,877)
			216,314,200	180,927,378
ወደፊት የሚከፈል የትርፍ ግብር ዕዳ	11.2		(546,119)	(2,487,832)
ትርፍ - ከትርፍ ግብር መጠባበቂያ በኋላ			215,768,082	178,439,546
ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ የዞረ			(53,942,020)	(44,609,887)
ትርፍ - ከትርፍ ግብር እና ከሕጋዊ መጠባበቂያ በኋላ			161,826,061	133,829,660
ካለፈው ዓመት የዞረ ያልተከፋፈለ ትርፍ			133,402,537	102,745,601
ሲቀነስ፣ ለባለ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ትርፍ			(133,402,537)	(102,745,601)
			161,826,061	133,829,660
ሲቀነስ፣ ለዲሬክተሮች ቦርድ የሚከፈል የትርፍ ድርሻ	22		(427,869)	(427,123)
ወደሚቀጥለው ዓመት የዞረ ያልተከፋፈለ ትርፍ			161,398,192	133,402,537
እያንዳንዱ አክሲዮን ያስገኘው ትርፍ	23		13.59	14.16
ብር 100 ዋጋ የተጻፈባቸው አክሲዮኖች ያስገኙት ትርፍ	23		54.36	56.65

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የገንዘብ ፍሰት መግለጫ
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ.ም. ሳለቀው ዓመት

	ብር	ብር	2002 ብር
ከ/ለመደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ የወጣ / የተገኘ የተጣራ ገንዘብ			
ለግብር መጠባበቂያ ከመቀነሱ በፊት የተገኘ ትርፍ		288,579,072	258,383,255
የእርጅና ተቀናሽና የማቋቋሚያ ወጪ	15,280,166		13,176,806
ለአጠራጣሪ ሌሎች ተሰብሳቢዎች መጠባበቂያ	511,353		6,739,377
ለአጠራጣሪ ብድሮች መጠባበቂያ	23,629,459		18,996,907
ቋሚ ዕቃዎች ሽያጭ	(354,639)		(653,647)
ከውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን ለውጥ የተገኘ ትርፍ	(85,381,411)		(128,745,904)
		(46,315,072)	(90,486,461)
ለሥራ እንቅስቃሴ ከዋለው ሀብት እና ዕዳ ለውጥ በፊት ከመደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ የተገኘ		242,264,000	167,896,794
በመሰብሰብ ላይ ያሉ ሂሳቦች ቅናሽ	(5,579,693)		95,041,824
የሌሎች ተቀማጮች እና ቅድሚያ ክፍያዎች ጭማሪ	(9,849,802)		(17,118,016)
የብድሮች (ጭማሪ)/ቅናሽ	(615,726,829)		(304,511,440)
የሌሎች ሀብቶች ቅናሽ/(ጭማሪ)	(31,490,857)		(10,845,997)
የደንበኞች ተቀማጭ ጭማሪ	695,986,690		936,411,269
የሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ጭማሪ/(ቅናሽ)	(39,538,053)		31,256,700
የመተማመኛ፣ የዱቤ ሠነዶች ቅድሚያ ክፍያ ጭማሪ	68,344,728		(66,917,242)
ለ/ከመደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ ከወጣው በላይ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ		62,146,184	663,317,098
ለትርፍ ግብር የተከፈለ		(77,432,652)	(55,734,701)
ከመደበኛ የሥራ እአንቅስቃሴ የተገኘ ገንዘብ		226,977,532	775,479,191
ከ/ለኢንቨስትመንት እአንቅስቃሴ የተገኘ/የወጣ ገንዘብ			
ከቋሚ ዕቃዎች ሽያጭ	491,723		658,362
ለቋሚ ዕቃዎች ግዢ	(24,884,109)		(23,265,812)
ፕሮጀክት ላይ የተደረገ ኢንቨስትመንት	(40,881,110)		(25,734,766)
ኢንቨስትመንት	(1,258,000)		-
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰነድ ግዢ	(644,630,000)		(816,603,000)
ለ/ከኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ (ከተገኘው በላይ የወጣ)/ከወጣው በላይ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ		(711,161,496)	(864,945,216)
ከ/ለፋይናንስ እንቅስቃሴ የተገኘ/የወጣ ገንዘብ			
ከአክሲዮን ሽያጭ	71,588,304		-
ለባለአክሲዮኖች የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ	(45,154,664)		(101,903,711)
ለዳይሬክተሮች የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ	(427,123)		(3,468,414)
ከ/ለፋይናንስ እንቅስቃሴ ከወጣው በላይ የተገኘ / (ከተገኘው በላይ የወጣ) የተጣራ ገንዘብ		26,006,517	(105,372,125)
ከውጪ ገንዘብ ምንዛሪ ተመን ለውጥ የተገኘ ትርፍ		85,381,411	128,745,904
የዓመቱ የተጣራ የገንዘብ ዕድገት		(372,796,037)	(66,092,246)
በዓመቱ መጀመሪያ የነበረ ገንዘብ		2,895,908,763	2,962,001,009
በዓመቱ መጨረሻ የነበረ ገንዘብ		2,523,112,726	2,895,908,763

አቢሲንያ ባንክ አ.ማ.
የባለአክሲዮኖችን ሀብት ላይ የተከናወኑ ለውጦችን የሚያሳይ ዝርዝር
ሰኔ 23 2004 ዓ. ም. ሳለቀው ዓመት

	የተከፈለ ካፒታል	በአክስዮን ሽያጭ ዋጋ ብልጫ የተሰበሰበ	ሕጋዊ መጠባበቂያ	ልዩ መጠባበቂያ	ያልተከፈለ ትርፍ	ጠቅላላ
እ.ኤ.አ. ሐምሌ 1 ቀን 2010 የነበረ	315,000,000	2,827,540	138,999,707	25,918,839	102,745,601	585,491,687
የተፈፀመ የትርፍ ክፍያ	-	-	-	-	(101,903,711)	(101,903,711)
ከአክስዮን ዋጋ በብልጫ የተሰበሰበ	-	-	-	-		-
ወደ ተከፋይ ሂሣብ የዞረ የትርፍ ክፍያ	-	-	-	-	(841,890)	(841,890)
የተጨመሩ አዳዲስ አክሲዮኖች	-	-	-	-		-
የዓመቱ የተጣራ ትርፍ	-	-	-	-	178,439,547	178,439,547
የቦርድ ዳይሬክተሮች ድርሻ ከተጣራው ትርፍ ላይ	-	-	-	-	(427,123)	(427,123)
ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ የዞረ	-	-	44,609,887	-	(44,609,887)	-
እ.ኤ.አ. ሐምሌ 1 ቀን 2011 የነበረ	315,000,000	2,827,540	183,609,594	25,918,839	133,402,537	660,758,510
ለባለአክሲዮኖች የተመደበ የትርፍ ክፍያ	-	-	-	-	(41,141,908)	(41,141,908)
ወደተከፋይ ሂሣብ የዞረ የትርፍ ክፍያ	-	-	-	-	-	-
ለአክሲዮን ማሳደጊያ የዋለ በ2011	92,260,629	-	-	-	(92,260,629)	-
ለአክሲዮን ማሳደጊያ የዋለ በ2010	48,768	-	-	-	-	48,768
የቦርድ ዳይሬክተሮች ድርሻ ከተጣራው ትርፍ ላይ	-	-	-	-	(427,869)	(427,869)
የተጨመሩ አዳዲስ አክሲዮኖች	71,588,305	-	-	-	-	71,588,305
የአመቱ የተጣራ ትርፍ	-	-	-	-	215,768,082	215,768,082
ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ የዞረ	-		53,942,020		(53,942,020)	-
እ.ኤ.አ. ሐምሌ 1 ቀን 2012 ያለ	478,897,702	2,827,540	237,551,614	25,918,839	161,398,192	906,593,888

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኀበር
የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

1. **የባንኩ አመሠራረት**

አቢሲንያ ባንክ የባንክን የሥራ ሂደት ስለመፍቀድ እና ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/94 እና በ1960 በታወጀው የንግድ ሕግ መሠረት ሕጋዊ ምዝገባና የሥራ ፍቃድ በማግኘት እ.ኤ.አ. በ1996 የተመሠረተ ባንክ ነው። ባንኩ በመላ የሐገሪቱ ክልሎች 63 ቅርንጫፎች አሉት።

2. **ዋና ዋና የሂሣብ ፖሊሲዎች**

ባንኩ የሚጠቀምበት ዋና ዋና የሂሣብ መርሆዎች ባለፈው ዓመት በተጣጣመ መልኩ ሲሰራበት የቆየ አሠራር ሲሆን ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሀ/ **ለሂሣብ አዘገጃጀት መሠረት የሆነ**

የሂሳብ መግለጫዎቹ የተዘጋጁት በየሂሳብ እንቅስቃሴዎቹ ወቅት በነበረው የዋጋ ተመን እንዲሁም አጠቃላይ ተቀባይነት ባላቸው የሂሳብ መርሆዎችና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ህግጋትና ደንቦች ላይ በመመርኮዝ ነው።

ለ/ **ፋይናንሺያል ኢንስትሩመንት (ሃብት እና ዕዳዎች)**

i. **አመዳደብ**

የፋይናንሺያል ኢንስትሩመንት ምንጭ የሚባሉት ከሌላ ወገን ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት የባንኩ ሃብት እና የባንኩ ዕዳዎች የሆኑ ጉዳዮች ናቸው። የባንኩ ቋሚ ሃብት፣ የወደፊት ዕዳዎች፣ ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሳቦች በስተቀር በባንኩ የሃብትና ዕዳ መግለጫ የተመዘገቡ ሁሉ የባንኩ ፋይናንሺያል ኢንስትሩመንት ናቸው።
ባንኩ ለተበዳሪዎች የሚሰጠው ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች ዋነኛው የባንኩ ሃብቶች ናቸው። የብድሩ ገንዘብ የሚገኘው ከአስቀማጭ ደንበኞች፣ በሌሎች ባንኮች ካለተቀማጭ እና ቀደም ሲል ከባንኩ ከተበደሩት ደንበኞች የሚሰበሰብ ይሆናል።

ii. **ሃብት እና ዕዳዎች የሚመዘገቡበት ሁኔታ**

ባንኩ ሃብት እና ዕዳውን በባንኩ ሃብት እና ዕዳ መግለጫ ባለሃብት ወይም ባለዕዳ ከሆነበት ቀን አንስቶ መዝግቦ ይይዛል። በሃብቱ ላይ የሚከሰት የዋጋ ልዩነት ከዚህ ቀን ጀምሮ በትርፍነት ወይም በኪሣራ ይመዘግባል።
ባንኩ ከብድር ጋር በተያያዘ በውሉ መሠረት ዋናውን ገንዘብ እና ወለድ የመቀበል መብት ይኖረዋል። በዚህ መሠረት ከብድሩ ጋር ተያይዞ ያለውን ጥቅም ይቆጣጠራል። ባንኩ ብድርን መዝግቦ የሚይዘው ብድሩ ለደንበኛው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው። ነገር ግን በሂደት ላይ ያለ የብድር ጥያቄ የባንኩ ሃብት ሆኖ በባንኩ የሃብትና ዕዳ መግለጫ ላይ አይመዘገብም።

iii/ **ሃብት እና ዕዳዎች የማይመዘገቡበት ሁኔታ**

ባንኩ በሁሉም ሃብቶች ላይ ያለው የመቆጣጠር መብት/ሥልጣን በተለያየ ምክንያት በሚያጣበት ጊዜ፣ የባንኩ ሃብት ሆነው አይመዘገቡም። ዕዳዎች የተከፈሉ እንደሆነ እንደ ዕዳ አይመዘገቡም።

iv/ **የሃብት እና ዕዳ መለኪያ**

ባንኩ ሁሉንም ሃብት እና ዕዳ የሚለካው በወቅቱ በሚኖራቸው ዋጋ እና ተያያዥ ወጪዎችን በመጨመር ነው።

ሐ/ ብድር እና ቅድሚያ ክፍያዎች

ብድርና ቅድሚያ ክፍያዎች የባንኩ ፋይናንሺያል ኢንስትሩመንት ሲሆኑ የሚፈጠሩትም ባንኩ ለደንበኞች ገንዘብ ሲያበድር ነው፡፡ ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች በሂሳብ ውስጥ የተመዘገበው አስፈላጊው የብድር መጠባበቂያ ከተቀነሰ በኋላ ነው፡፡ ባንኩ ለብድሮች መጠባበቂያ የሚይዘው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/43/2008 መሠረት ነው፡፡ መመሪያውም ብድሮችንና ቅድሚያ ክፍያዎችን በሚከተለው መልኩ ይመድባል:-

i/ <u>አስተማማኝ ብድሮች</u>

በዚህ ምድብ ውስጥ የሚመደቡ ብድሮች ተበዳሪው በወቅቱ ያለው የገንዘብ አቅም እና ወደፊትም ካለምንም እንከን ብድሮቹን የመክፈል አቅም ሲኖረው ነው፡፡ እንዲሁም ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች በገንዘብ እና ገንዘብ አከል ንብረቶች ዋስትና የተሰጡ እንደሆነ የብድሩ አከፋፈል ሁኔታ ከግምት ሳይገባ ብድሮቹ አስተማማኝ ብድሮች በሚል ይመደባሉ፡፡

ii/ <u>ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ብድሮች</u>

ማንኛውም ብድሮች እና ቅድሚያ ክፍያዎች ሳይከፈሉ ከ30 ቀናት በላይ እና ከ90 ቀናት የሚያንስ ከሆነ በዚህ ምድብ ሥር ይካተታሉ፡፡

iii/ <u>በከፊል አጠራጣሪ ብድሮች</u>

መመለሳቸው አጠራጣሪ የሆኑ ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች ሆነው ሳይከፈሉ ከ90 ቀናት በላይ እና ከ180 ቀናት በታች ከሆኑ በዚህ ምድብ ሥር ይካተታሉ፡፡

iv/ <u>አጠራጣሪ ብድሮች</u>

መመለሳቸው አጠራጣሪ የሆኑ ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች ሆነው ሳይከፈሉ ከ180 ቀናት በላይ እና ከ360 ቀናት በታች ከሆኑ በዚህ ምድብ ይመደባሉ፡፡

v/ <u>የተበላሹ ብድሮች</u>

መመለሳቸው አጠራጣሪ የሆኑ ብድሮችና ቅድሚያ ክፍያዎች ሆነው ሳይከፈሉ ከ360 ቀናት በላይ ያለፋቸው ከሆኑ በዚህ ምድብ ሥር ይካተታሉ፡፡
በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ለብድሮች የሚያዘው መጠባበቂያ ምጣኔ /%/ እንደሚከተለው ይሆናል:-

ተ.ቁ.	የብድሩ ምድብ	የሚያስፈልገው የብድር መጠባበቂያ /በመቶኛ/
1	አስተማማኝ ብድሮች	በሚሰበሰበው ጠቅላላ ብድር ላይ /1%/
2	ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ብድሮች	በሚሰበሰበው ጠቅላላ ብድር ላይ /3%/
3	በከፊል አጠራጣሪ ብድሮች	በሚሰበሰበው ጠቅላላ ብድር ላይ /20%/
4	አጠራጣሪ ብድሮች	በሚሰበሰበው ጠቅላላ ብድር ላይ /50%/
5	የተበላሹ ብድሮች	በሚሰበሰበው ጠቅላላ ብድር ላይ /100%/

ማሳሰቢያ፣

የተጣራ የብድር መጠን ማለት፣ በሚሰበሰበው ጠቅላላ የብድር መጠን ላይ መያዣዎች የሚያስገኙት የተጣራ ገንዘብ ከተቀነሰ በኋላ ነው።

መ/ ቋሚ ንብረቶች

ባንኩ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እ.ኤ.አ. እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ድረስ ቀጥተኛ የሆነ የእርጅና አቀናነስ ስርዓት ይከተል ነበር። ነገር ግን አዲስ በወጣው የግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 መሠረት ባንኩ የእርጅና ቅናሽ ስርዓቱን ወደ ጥቅል የእርጅና አቀናነስ ስርዓት በመቀየር እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ሲጠቀምበት ቆይቷል። በአሁኑ ጊዜ የእርጅና አቀናነስ ስርዓቱን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ካላቸው የሂሳብ መርሆዎች ጋር ለማጣጣም ወደ ቀጥተኛ የእርጅና አቀናነስ ስርዓት ተለውጦ የሂሳብ ማስተካከያ ተከናውኗል።

i/ ቋሚ ዕቃዎች በሂሳብ የተመዘገቡት በተገዙበት ዋጋ ላይ የእርጅና ተቀናሻቸው ከተሰላ በኋላ ነው። የእርጅና ተቀናሹ ቀጥተኛ በሆነ አቀናነስ ስርዓት የተሰላ ሲሆን፣ ምጣኔው እንደሚከተለው ነው፡-

	በመቶኛ (%)
ተሽከርካሪ መኪኖች	20%
የቢሮ መሣሪያዎች እና ዕቃዎች	10%
ኮምፒዉተሮች	10%
ሕንፃዎች	5%

በግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 መሠረት ለትርፍ ግብር ስሌት አስፈላጊው የሂሣብ ማስተካከያ ተከናውኗል። /ማብራሪያ 9/

ሠ/ የገቢዎች አመዘጋገብ

የወለድ ገቢና ወጪዎች በገቢነትና በወጪነት የሚመዘገቡት አገልግሎቱ እንደተሰጠ ወይም አገልግሎቱን እንደተቀበለ ነው። ነገር ግን ተሰብሳቢነታቸው አጠራጣሪ ለሆኑ ብድሮች ወለድ ተሰልቶና በማቆያ ሂሳብ ተይዞ በገቢነት የሚመዘገበው ሲሰበሰብ ብቻ ነው።

ረ/ <u>የውጭ ምንዛሪዎች</u>

የውጭ ሀገር ገንዘቦችን የሚመለከቱ እንስቅቃሴዎች ወደ ብር የሚመነዘሩት በየዕለቱ አግባብ ባላቸው ተመኖች ነው ። በየቀኑ መጨረሻ የውጪ ሀገር ገንዘቦች የብር ምንዛሪያቸው የሚሰላው በዕለቱ ባለው የመግዣ ተመን ሆኖ የተገኘው ትርፍ ወይም ኪሣራ በትርፍና ኪሣራ ሂሣብ ይመዘገባል።

ሰ/ <u>የወደፊት ወጪዎች</u>

እነዚህ ወጪዎች የሚያካትቱት ባንኩ የተቀናጀ የባንክ ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ለማድረግ እያወጣው ያለውን ወጪ ነው።

ሸ/ <u>የቦታ ይዞታ</u>

ባንኩ ከናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር በመሆን ስፋቱ 1,248 ካሬ ሜትር የሆነና ለ55 ዓመታት የሚቆይ የመሬት ይዞታ በሊዝ ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ተረክቧል።

ቀ/ <u>ለባንኩ ሠራተኞች የሚከፈል ጉርሻ</u>

ለሠራተኞች የሚሰጠው ጉርሻና የአገልግሎት ካሣ ክፍያ በወጪነት የሚመዘገቡት ክፍያ ሲፈፀም ነው።

በ/ <u>ከወለድ የሚገኝ ገቢ</u>

ከውጭ ሀገር ለሚገዙ ዕቃዎች ከሚሰጥ ጊዜያዊ ብድር የሚገኘው ወለድ በገቢነት የሚመዘገበው ብድሩ ሲሰበሰብ ነው።

ተ/ <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰነድ ግዢ</u>

ባንኩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር MFA/NBEBills/001/2011 መሠረት በአምስት አመት የሚመለሱ ሰነዶች የገዛበት ነው።

ቸ/ <u>ሌሎች ኢንቨስትመንቶች</u>

ባንኩ ኢትዮ-ስዊች አ.ማ. ላይ ከተመዘገበው አክሲዮን ውስጥ 25% ለሚሆነው ብር 5,030,000.00 የከፈለው ነው።

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

3. ተቀማጭና ቅድሚያ ክፍያዎች

		2003
	ብር	ብር
በቅድሚያ የተከፈለ ኪራይ	42,354,103	32,504,301
ለኪራይ መያዣ ተቀማጭ	2,133,560	2,133,560
	44,487,663	34,637,861
ሲቀነስ፣ ለአጠራጣሪ ሌሎች ተሰብሳቢዎች መጠባበቂያ	(2,000,000)	(2,000,000)
	42,487,663	32,637,861

4. ለደንበኞች የተሰጡ ብድሮች

		2003
	ብር	ብር
ለሀገር ውስጥ ንግድና አገልግሎቶች	1,689,161,217	1,145,674,315
ለገቢ ንግድ	486,886,861	435,688,699
ለግንባታ ሥራዎች	528,918,800	527,482,526
ለትራንስፖርት	86,923,701	115,793,020
ለኢንዱስትሪ	235,927,894	307,759,576
ለወጪ ንግድ	552,542,183	480,430,037
በገቢ ንግድ ሠነዶች መያዣነት	39,549,272	24,212,035
በሸቀጣ ሸቀጦች መያዣነት	106,608,809	137,391,645
ወደ ክስ የተመሩ	40,029,384	67,031,821
ለግል	72,554,259	41,178,788
ለእርሻ	4,350,218	5,349,149
በወጪ ንግድ ዕቃዎች ሠነድ መያዣነት	33,265,288	17,743,363
በልማት ባንክ መያዣነት ለወጪንግድ	4,425,731	-
በሽያጭ ውል ሰነድ መያዣነት	16,263,086	9,952,958
	3,897,406,701	3,315,687,932
ሲቀነስ: ለአጠራጣሪ ብድሮች መጠባበቂያ (ማብራሪያ 15)	(100,101,041)	(110,479,642)
	3,797,305,660	3,205,208,290

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

5. ሌላ ሀብት

		2003
ለሽያጭ የሚውሉ የተበዳሪ ደንበኞች ንብረቶች	43,569,423	43,316,202
የጽሕፈት መሣሪያዎችና ሌሎች በመጋዘን ያሉ ዕቃዎች	3,736,461	3,168,301
ለሕክምና የተከፈለ ተሰብሳቢ ሂሣብ	841,708	665,318
በመጋዘን ያሉ ቋሚ ዕቃዎች	9,078,062	4,685,094
ወደፊት ለሚከፈቱ ቅርንጫፎች ማቋቋሚያ ወጪዎች	-	8,390,863
ወደፊት ከሚሰበሰቡ ገቢዎች	41,169,089	4,746,150
ልዩ ልዩ ተሰብሳቢ ሂሣቦች	28,292,861	30,224,819
	126,687,604	95,196,747
ሲቀነስ፣ ለአጠራጣሪ ሌሎች ተሰብሳቢዎች መጠባበቂያ	(15,608,388)	(15,097,035)
	111,079,216	80,099,712

6. የቦታይዞታ

	በዓመቱ መጀመሪያ የነበረ ብር	የተጨመረ ብር	በዓመቱ መጨረሻ የታየ ብር
በሊዝ ለተያዘ መሬት የተከፈለ ወጪ	566,920	-	566,920
በሊዝ ከተያዘው መሬት ዋጋ ወደ ወጪ የዞረ	(98,862)	9,959	(108,820)
የተጣራ በመዝገብ የተመለከተ ዋጋ	468,058	9,959	458,099

7. የወደፊት ወጪዎች

	በዓመቱ መጀመሪያ የነበረ ብር	የተጨመረ ብር	በዓመቱ መጨረሻ የታየ ብር
የወጣ ወጪ	27,379,681	40,881,110	68,260,791

8. ቋሚ ሀብት

	በዓመቱ መጀመሪያ የነበረ ብር	የተጨመረ ብር	በሽያጭ የተወገደ ብር	የሂሳብ ማስተካከያዎች/ የተቀነሰ ብር	በዓመቱ መጨረሻ የታየ ብር
ዋጋ					
ሕንፃዎች	38,785,664	-	-	-	38,785,664
ተሽከርካሪ መኪኖች	48,956,807	10,812,994	(496,208)	-	59,273,592
የቢሮና ሌሎች መሣሪያዎች	22,207,859	4,337,683	-	-	26,545,542
የቢሮ ዕቃዎች	24,099,904	4,790,383	(160,064)	-	28,730,223
ኮምፒውተሮችና ዕቃዎቻቸው	15,883,806	4,636,698	-	-	20,520,504
በግንባታ ላይ ያለ ሕንፃ	542,776	306,350	-	-	849,126
	150,476,816	24,884,109	(656,273)		174,704,652
የእርጅና ተቀናሽ					
ሕንፃዎች	8,958,200	1,939,283	-	-	10,897,483
ተሽከርካሪ መኪኖች	28,676,940	7,426,394	(470,965)	-	35,632,369
የቢሮና ሌሎች መሣሪያዎች	7,377,582	2,303,361	-	-	9,680,943
የቢሮ ዕቃዎች	12,247,955	2,025,668	(48,225)	-	14,225,398
ኮምፒውተሮችና ዕቃዎቻቸው	7,135,659	1,575,501	-	-	8,711,160
	64,396,336	15,270,207	(519,190)		79,147,353
የተጣራ በመዝገብ የተመለከተ ዋጋ	86,080,480				95,557,299

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

9. የደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ

	በተንቀሳቃሽ ሂሣብ ብር.	በቁጠባ ሂሣብ ብር.	በጊዜ ገደብ የተቀመጠ ሂሣብ ብር.	ድምር ብር.	2003 ድምር ብር.
የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ	1,389,550,517	4,721,334,421	63,074,567	6,173,959,505	5,619,072,863
የህብረት ሥራ ማህበርና ሌሎች ማህበራት	62,404,673	184,744,061	16,214,021	263,362,755	247,000,688
የሀገር ውስጥ ባንኮች	40,046,641	7,397,414	135,254,593	182,698,648	45,684,228
ነዋሪ ላልሆኑ ወደ ውጪ ምንዛሪ የሚለወጡ የብር ሂሣቦች	33,194,808	-	-	33,194,808	42,277,975
ሕዝባዊ ድርጅቶች	16,119,216	10,233,231	2,491,355	28,843,801	35,479,208
ነዋሪ ላልሆኑ ወደ ውጪ ምንዛሪ የማይለወጡ የብር ሂሣቦች	11,766,704	-	-	11,766,704	6,715,545
ነዋሪ ላልሆኑ የውጪ ምንዛሪ ሂሣቦች	61,711,141	-	-	61,711,141	59,861,825
ነዋሪ ለሆኑ የውጪ ምንዛሪ ሂሣቦች	15,708,226	-	-	15,708,226	19,166,566
በሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም.	1,630,501,927	4,923,709,126	217,034,535	6,771,245,588	6,075,258,898
በሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ. ም.	1,591,369,708	4,422,862,487	61,026,703	6,075,258,898	

10. ሌሎች ዕዳዎች

	ብር	2003 ብር
የክፍያ ትዕዛዝ ሠነዶች	187,193,385	219,063,257
የታገዱ ሂሣቦች	37,566,286	43,736,491
በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ለማስተላለፍ ባንኩ የተረከበው ገንዘብ	19,474,917	20,652,285
የቦርድ ዳይሬክተሮች አበል	449,165	448,419
ለባለ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ትርፍ	10,038,395	14,099,919
ለጊዜ ገደብ ተቀማጭ ተከፋይ ወለድ	7,564,154	1,755,552
የቆዩ የክፍያ ትዕዛዞች ክፍያዎች	6,013,306	4,751,293
የምንዛሪ አገልግሎት ክፍያና የጨረታ መያዣ	10,325,079	7,603,759
ለዓመት ፈቃድ ክፍያ	14,642,801	11,382,092
ለቴምብር ቀረጥ	752,800	1,033,060
የሥራ ግብር	1,304,827	841,259
የወለድ ሽያጭ ታክስ	575,800	1,240,688
ለተሰጠ ዋስትና መያዣ	5,887,147	5,308,860
የሣጥን ቁልፍ ኪራይ	108,000	109,400
የኦዲተሮች አበል	120,000	120,000
ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሣቦች	10,985,532	24,448,577
በህግ ሂደት ላይ ላሉ ጉዳዮች የተያዘ መጠባበቂያ	2,279,667	2,285,251
	315,281,331	358,880,162

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

11. የትርፍ ግብር መጠባበቂያ

የዚህ ሂሣብ ዝርዝር እንደሚከተለው ነው::

			2003
		ብር	ብር
ካለፈው ዓመት የዞረ		77,416,189	55,695,014
ሲቀነስ፡ በዚህ ዓመት የተከፈለ		(77,416,189)	(55,695,014)
የዓመቱ ትርፍ ግብር		-	-
ግብር ከመቀነሱ በፊት የተገኘ ትርፍ		288,579,072	258,383,255
ሲቀነስ፣ ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች			
የእርጅና ተቀናሽ በግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 መሠረት(ከታች 11.1 ይመልከቱ)	16,735,963		14,233,891
ከምንጩ ግብር የተከፈለበት ገቢ	41,477,506		4,946,703
በውጭ ሀገር ባንኮች ከተቀመጠ ገንዘብ የተገኘ ወለድ	1,486,420		1,412,028
ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ	354,639		653,646
		(60,054,528)	(21,246,268)
ሲደመር፣			
ለአጠራጣሪ ሌሎች ተሰብሳቢዎች መጠባበቂያ	511,353		6,739,377
የእርጅና ተቀናሽ በባንኩ ፓሊሲ መሠረት	15,270,207		13,166,847
ስጦታ	96,810		20,000
መስተንግዶ	978,406		887,707
		16,856,777	20,813,931
ግብር የሚከፈልበት የዓመቱ ትርፍ		245,381,320	257,950,918
የትርፍ ግብር /30%/		73,614,396	77,385,275
ሲደመር፣ 5% በውጪ ሀገር ባንኮች ከተቀመጠ ገንዘብ የተገኘ ወለድ ላይ የትርፍ ግብር መጠባበቂያ		74,321	70,601
ሲቀነስ፣ የቅድሚያ ግብር ክፍያ		(1,423,845)	-
		72,264,872	77,455,876
ሲቀነስ፣ የቅድሚያ ግብር ክፍያ		(16,463)	(39,687)
የትርፍ ግብር መጠባበቂያ		72,248,409	77,416,189

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

11.1 የእርጅና ተቀናሽ በግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 መሠረት

	ብር	ብር
ህንፃ		
ዋጋ	38,785,664	
ሲቀነስ: ካባለፈው ዓመት የዞረ የእርጅና ተቀናሽ	(8,958,200)	
የዚህ ዓመት የእርጅና ተቀናሽ	(1,939,283)	1,939,283
የእርጅና ቅናሽ መሠረት	38,785,664	

ኮምፒውተሮችና ዕቃዎቻቸው

	ብር	ብር
የእርጅና ቅናሽ መሠረት ወደዚህ ዓመት የዞረ	5,282,891	
ሲደመር: የዚህ ዓመት ተጨማሪ ግዥ	4,636,698	
የእርጅና ቅናሽ መሠረት	9,919,589	
የእርጅና ቅናሽ 25%	(2,479,897)	2,479,897
የተጣራ ዋጋ	7,439,692	
ሌሎች ዕቃዎች		
የእርጅና ቅናሽ መሠረት ወደዚህ ዓመት የዞረ	42,134,578	
ሲደመር: የዚህ ዓመት ተጨማሪ ግዥ	19,941,060	
ሲቀነስ: በሽያጭ የተወገዱ ዕቃዎች	(491,723)	
የእርጅና ቅናሽ መሠረት	61,583,915	
የእርጅና ቅናሽ 20%	(12,316,783)	12,316,783
የተጣራ ዋጋ	49,267,132	
አጠቃላይ የእርጅና ተቀናሽ በግብር አዋጅ መሠረት		16,735,963

የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ላሉት የበጀት ዓመታት የትርፍ ግብር ምርመራ አድርጎ ለባንኩ የሰጠው የግብር ማስታወቂያ የለም፣ ሆኖም እስከ ሰኔ 23 ቀን 1995 ዓ. ም. ለነበሩት የሂሣብ ዘመናት ባንኩ ባቀረበው ሂሣብ መሠረት የተከፈለው ግብር የመጨረሻ ክፍያ እንደሚሆን ታውቋል።

11.2 ወደፊት የሚከፈል የትርፍ ግብር ዕዳ

		2003
	ብር	ብር
የተጣራ የመዝገብ ዋጋ በባንኩ ፖሊሲ መሠረት	94,708,173	85,537,704
የእርጅና ተቀናሽ መሠረት /በግብር አዋጁ/	84,595,005	77,244,932
ጊዜያዊ ልዩነት	10,113,168	8,292,772
ወደፊት የሚከፈል የትርፍ ግብር ዕዳ 30%	3,033,950	2,487,832

12 ካፒታል

ዓይነት	የአክሲዮኖች ብዛት	የተጻፈበት ዋጋ ብር	2003 ጠቅላላ ዋጋ ብር	2003 ጠቅላላ ዋጋ ብር
የተፈቀደ	25,200,000	25	630,000,000	630,000,000
የተፈረመ እና የተከፈለ	19,155,908	25	478,897,703	315,000,000

በዓመቱ ለነባር ባለ አክሲዮኖች ባንኩ እያንዳንዳቸዉ 25 ዋጋ ያላቸዉ 6,555,908 ሽሮች ሸጧል ።

13 ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ

	ብር	2003 ብር
በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የነበረ	183,609,594	138,999,707
ከዓመቱ ትርፍ የዞረ (215,768,082 @ 25%)	53,942,020	44,609,887
	237,551,614	183,609,594

ከትርፍ ግብር በኃላ ካለው ቀሪ ላይ 25% ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ በብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የተሰላ ነው

14 ልዩ የመጠባበቂያ

	ብር	2003 ብር
በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የነበረ	25,918,839	25,918,839
ከዓመቱ ትርፍ የዞረ	-	-
	25,918,839	25,918,839

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

15 ለደንበኞች ለተሰጡ አጠራጣሪ ብድሮች መጠባበቂያ

የዚህ ሂሣብ ዝርዝር እንደሚከተለው ነው።

			2003
	ብር	ብር	ብር
ካለፈው ዓመት የዞረ		110,479,642	233,550,703
ሲቀነስ:			
የተሰረዙ ለደንበኞች የተሰጡ ብድሮች		(34,008,060)	(142,067,968)
		76,471,582	91,482,735
ሲደመር: የተበላሹ ብድሮች የተያዘ መጠባበቂያ		23,629,459	18,996,907
		100,101,041	110,479,642

16 ከወለድ የተገኘ ገቢ

		2003
	ብር	ብር
ወለድ: በጊዜ ገደብ ከተሰጠ ብድር	363,238,118	277,684,641
: ከኦቨር ድራፍት	73,021,181	71,483,582
: ከገቢና ወጪ ንግድ	6,499,957	10,824,777
: ወደክስ ከተመሩ ብድሮች	11,764,215	981,096
	454,523,471	360,974,096
ከውጭ ሀገር ባንኮች ተቀማጭ	1,486,420	1,412,028
ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰነድ ግገር	36,329,860	4,746,150
ከ ግምጃ ቤት ሰነድ	585,565	
ከሀገር ውስጥ ባንኮች ተቀማጭ	4,562,082	4,946,703
	497,487,397	372,078,977

17 ከውጪ ምንዛሪ ተመን ለውጥ የተገኘ ትርፍ

		2003
	ብር	ብር
ከውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ የተገኘ ትርፍ	131,213,063	267,433,845
ሲቀነስ: ከውጭ ምንዛሬ ተመን ለውጥ የተገኘ	(45,831,652)	50,195,160
ኪሳራ		
ከንፋስ አመጣሽ ገቢ ተከፈለ		88,492,781
ታክስ	(45,831,652)	138,687,941
	85,381,411	128,745,904

ባንኩ ባለፈው አመት ከብር ምንዛሬ ለውጥ መውረድ ጋር በተገናኘ ባገኘው ገቢ ላይ 75% የንፋስ አመጣሽ ግብር ብር 88,492,781 በደንብ ቁጥር 693/2010 መሠረት ከፍሏል።

18 ከኮሚሽን የተገኘ ገቢ

		2003
	ብር	ብር
ከመተማመኛ የዱቤ ሠነዶች:- ከሀገር ውስጥና ከውጭ ንግድ ብድሮች	7,003,808	6,238,853
ከገንዘብ ማስተላለፍ:- በሀገር ውስጥና ውጪ ሀገር	12,043,719	9,581,017
ከዋስትና ሠነዶች	4,079,612	3,702,931
ከገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ ሠነዶች	1,009,498	1,378,028
ከመንገደኛ ቼኮችና ሌሎች	442,037	637,437
በመጣራት ላይ ካሉ ሠነዶች	1,156,667	1,037,044
	25,735,342	22,575,310

19 ልዩ ልዩ ገቢ

	ብር	2003 ብር
ለውጭ ንግድ ከተሰጡ የመተማመኛ የዱቤ ሠነዶች	14,792,653	14,073,095
ከኪራይ	549,054	741,916
ከስልክ፣ ከቴሌግራም፣ ከቴሌክስና ከፋክስ	5,630,212	5,404,142
ሌሎች	6,877,702	6,961,886
ከንብረት ሽያጭ የተገኘ ገቢ	354,639	653,647
ከተሸጡ የተበዳሪ ደንበኞች ንብረቶች የተገኘ ገቢ	-	224,840
	28,204,260	28,059,526

ሌሎች ገቢዎች ወስጥ ከገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ ሰነዶች የተመለሰ ብር 3,124,952.71 ተሰርዞ ከነበረ ወስጥ የተመለሰ ነው

20 የወለድ ወጪ

	ብር	2003 ብር
ለቁጠባ ሂሣቦች	194,215,476	159,141,550
በጊዜ ገደብ ለተቀመጡ ሂሣቦች	14,235,990	4,576,076
	208,451,466	163,717,626

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማኅበር

የሂሣብ መግለጫዎች ማብራሪያዎች
ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ. ም. ላለቀው ዓመት

21 የአስተዳደርና ሌሎች ወጪዎች

		2003
	ብር	ብር
ለቢሮ ኪራይ	29,603,326	22,669,601
ለእርጅና ተቀናሽ	15,270,207	13,166,847
ለፖስታ፣ ለስልክ፣ ለቴሌግራም፣ ለቴሌክስ / ፋክስ	4,577,097	4,516,838
ለጽሕፈት መሣሪያዎችና ለሕትመት	7,815,424	6,161,633
ለመጓጓዣ	6,645,784	5,595,444
ለማስታወቂያ	3,814,659	3,954,236
የመኪናና የመስተንግዶ አበል	1,319,972	1,202,665
ለጥገና	3,797,662	2,793,660
ለነዳጅና ቅባት	4,584,372	3,334,180
ለመድኅን	3,627,020	2,926,553
ለውሎ አበልና ለጉዞ	2,157,391	1,384,744
ለውጭ ሀገር ባንኮች አገልግሎት	987,213	813,056
ለስዊፍት አገልግሎት	527,764	590,523
ለውሃና ለመብራት	1,071,498	898,263
ለባለሙያዎች አገልግሎት	-	10,379
የማቋቋሚያ ወጪ	9,959	9,959
ለሥጦታና መዋጮ	120,941	217,200
ዓመታዊ ግብዣ	2,634,465	1,732,305
ለባንክ አገልግሎት	1,366,735	626,529
ለቦርድ ጽ/ቤት	54,000	54,000
ለአባልነትና ደንበኝነት	388,665	342,996
ለመስተንግዶ	978,406	887,707
ለቅርንጫፎች ምረቃ	395,358	575
ለሕግ ጉዳይ	54,375	56,448
ለይዞታ ማረጋገጫ ክፍያ	8,550	7,550
ለፅዳት መገልገያዎች	444,075	345,338
ለጉልበት ክፍያ	638,160	317,093
ለገንዘብ ዝውውር	322,676	223,399
ከቋሚ ንብረት ሽያጭ ኪሳራ	23,335	3,043,479
ልዩ ልዩ	2,077,082	1,168,965
	95,316,169	79,052,165

22 የዲሬክተሮች ቦርድ አበል

የዚህ ዓመት የዲሬክተሮች ቦርድ አበል ክፍያ የተሰላው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እ.ኤ.አ በጥር 15 2011 በወጣው መመሪያ ቁጥር SBB/49/2011 መሠረት ነው:: መመሪያውም አንድ የቦርድ አባል በዓመት የሚያገኘውን ጥቅም 50,000.00 ብር እንደማይበልጥ ይደነግጋል:: እንዲሁም የዚህ ዓመት የዲሬክተሮች ቦርድ ጥቅም በትርፍና ኪሣራ መግለጫው ላይ ተመልክቷል::

23 እያንዳንዱ አክሲዮን ያስገኘው ትርፍ

እያንዳንዱ አክሲዮን ያስገኘው ትርፍ የተሰላው ከግብር መጠባበቂያ በኋላ የሕጋዊ መጠባበቂያ ከመቀነሱ በፊት ከተገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ በዓመቱ ውስጥ በአማካይ በባለአክሲዮኖች በተከፈለው የአክሲዮኖች ብዛት በማካፈል ነው::

24 ሊከሰት የሚችል ዕዳ

		2003
	ብር	ብር
የዋስትና ሰነድ	140,901,145	64,603,373
የመተማመኛ የዱቤ ሰነድ	521,119,677	273,155,240
	662,020,822	337,758,613

		2003
	ብር	ብር
በእጅ ያለ የመጓጓዣ ቼኮች	175,853	64,780
	49,042,258	76,750,261
ለክፍያ የመጡ ሰነዶች - ከደንበኛ የሚሰበሰብ /አይ.ቢ.ሲ./	121,169,027	89,867,891
ከውጪ ባንኮች ሊጣሩ የተላኩ ዶክመንቶች	1,345,291	2,886,251
በማይሰበሰቡ ብድሮች ላይ የተሰላ ወለድ	63,103,222	63,493,235
የተሰረዙ ለደንበኞች የተሰጡ ብድሮች	197,772,673	163,764,613
የገንዘብ ከረጢቶች	802	5,720
	432,609,126	396,832,751

Bank of Abyssinia – Branches Address

No.	Branch Name	Telephone	Fax	P.O.Box
Addis Ababa				
1	Abba Koran	011-155 92 38	011-155 93 11	12947
2	Abba Mela	011-156 47 77	011-156 03 74	“
3	Abinet	011-278 13 07	011-278 13 05	“
4	Addisu Gebeya	011-127 54 06	011-127 54 03	“
5	Airport	011-618 52 33	011-618 52 55	“
6	Bole	011-551 18 22	011-551 31 17	“
7	Bole Medhanialem	011-661 14 59	011-661 14 72	“
8	Bomb Tera	011-213 00 92	011-213 01 03	“
9	Debebe H/Yohannes	011-663 89 54	011-663 89 53	“
10	Filwuha	011-551 41 30	011-550 04 82	“
11	Gerji	011-629 89 21	011-629 70 52	“
12	Gofa	011-416 95 40	011-416 95 49	“
13	Gotera	011-416 08 24	011-416 08 20	“
14	Guenet	011-552 37 81	011-552 37 69	“
15	Gullele	011-270 75 25	011-270 75 21	“
16	Kality	011-439 46 56	011-439 46 93	“
17	Lafto	011-419 82 80	011-419 82 81	“
18	Lambret	011-647 8190	011-647 81 94	“
19	Legahar	011-550 91 23	011-550 92 50	“
20	Megenagna	011-618 25 14	011-618 25 18	“
21	Merkato	011-869 00 43	-	“
22	Negadras	011-275 24 34	011-276 76 26	“
23	Olympia	011-554 67 26	011-554 67 23	“
24	Piassa (Arada)	011-157 32 26	011-157 97 13	“
25	Ragueal	011-277 92 07	011-277 79 79	“
26	Sidist Killo	011-123 64 93	011-122 56 58	“
27	Temenja Yaj	011-466 09 31	011-466 09 67	“
28	Urael	011-662 30 01	011-662 55 64	“
29	U.S. Embassy Branch	011-124 48 24	-	“
30	Kazanchis Branch	011-557 07 43	011-557 07 44	”
31	Sarbet Branch	011-320 42 25	011-320 42 21	”
32	Churchill Road Branch	011-155 71 11	011-155 72 37	”
33	C.M.C Branch	011-116 51 92/58		”

Bank of Abyssinia – Branches Address

No	Branch Name	Telephone	Fax	P.O.Box
Outlying				
1	Adama Menaharia	022-112 73 99	022– 112 74 23	1591
2	Adi-Haki	034-441 87 42	034-441 87 51	1803
3	Alemgena	011-387 02 68	011-387 12 86	460
4	Alula Abba Nega (Mekele)	034-440 73 77	034-440 73 80	1375
5	Arada (Nazareth)	022-112 35 85	022-112 39 90	81
6	Arba Minch	046-881 47 98	046-881 48 00	2002
7	Atse Zera Yakob (Debre Birhan)	011-681 39 58	011-681 39 61	405
8	Awassa	046-220 32 83	046-220 40 57	916
9	Bahir Dar	058-220 33 00	058-226 20 01	156
10	Bishoftu	011-433 31 34	011-433 30 16	1353
11	Bule Hora	046-443 08 99	046-443 08 96	101
12	Chagni	058-225 00 94	058-225 00 76	74
13	Debre Markos	058-771 65 20	058-771 33 87	160
14	Debre Tabor	058- 441 18 04	058-441 10 92	296
15	Dessie	033-112 32 57	033-112 32 56	899
16	Dilla	046- 331 24 69	046-331 39 40	507
17	Dire Dawa	025-111 89 32	025-111 89 34	1472
18	Harar	025-666 01 46	025-667 09 95	1689
19	Hossaena	046- 555 40 15	046-555 40 16	449
20	Humera	034-448 09 65	034-448 14 61	127
21	Jimma	047-111 58 63	047-111 58 64	1365
22	Modjo	022-116 17 31	022-116 17 49	536
23	Mota	058-661 15 64	058-661 04 05	124
24	Shashemene	046-110 15 25	046-110 15 19	1197
25	Teppi	047- 556 18 82	047-556 18 78	016
26	Tewodros (Gonder)	058-111 43 82	058-111 46 03	906
27	Finote Selam	058-775 13 13	058-775 14 28	243
28	Tabor	046- 221 08 84	046- 221 07 75	2068
29	Wolayita Sodo	046- 551 34 24	046- 551 34 05	113
30	Chiro	025- 551 17 39	025- 551 17 65	470

BANK OF ABYSSINIA - BRANCH LOCATIONS

አቢሲንያ ባንክ
BANK OF ABYSSINIA



አቢሲንያ፣ የትጉሃን መናኸሪያ!

አቢሲንያ ባንክ አ.ማ.
BANK OF ABYSSINIA S.C.

ስልክ፡ +251 11 551 4130/ 515 9966
ፋክስ፡ +251 11 551 1575/ 551 0409
ኢ-ሜይል abyssinia@ethionet.et
ዌብሳይት፡ www.bankofabyssinia.com
SWIFTABYSETTA የፖ.ሣ. ቁጥር 12947
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

Designed & Printed by:- www.masterprintingpressplc.com